# ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፓብሊክ

ርዕሰ ብሄር፤ ሳህለወርቅ ዘውዴ
ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ዐብይ አህመድ

የጸጥታ ሀይላት ከመጠን ያለፈ እና አንዳንዴም ጭካኔ የተሞላበት ሀይል ተጠቅመዋል፤ ያለፍርድ ግድያዎችንም ፈጽመዋል። ብሄርን መሰረት አድርገው ጥቃት በሚፈጽሙ ታጣቂ ቡድኖችና ሚሊሻዎች አማካይነት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል። ንብረቶችም ወድመዋል። የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች ለእስር ተዳርገዋል።

## ዳራ

በተደጋጋሚ ዘርን/ብሄርን መሰረት አድርጎ የሚከሰተው አለመረጋጋትና ሁከት ወደ ፖለቲካዊ ጽንፈኝነት አምርቶ በ2011 ዓ.ም የተጀመረው የፖለቲካና የሰብዓዊ መብትን የማክበር ለውጥ ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኗል። ጥቅምት 29፣ 2013 ዓ.ም በትግራይ ክልል የተጀመረው ግጭት፣ የኢትዮጲያ ፌደራላዊ መንግስት፣ በትግራይ ክልል መንግስት ላይ (የሀይል) እርምጃ እንዲወስድ ምክንያት ሆኗል። ገና ግጭቱ እንደተጀመረ፣ በአማራ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ የሚደገፈው የፌዴራሉ ጦር ሀይል በአንድ ወገን፣ የትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ በሌላ ወገን በመሰለፍ ተፋልመዋል።

## ያለፍርድ የተፈጸሙ ግድያዎች

ተከስትው የነበሩ ግጭቶችና አለመረጋጋቶችን ለመቆጣጠር፣ የጸጥታ ሀይላት ከመጠን ያለፈና፣ አንዳንዴም ጭካኔ የተሞላበት፣ ሀይልን ተጠቅመዋል።  በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል(ደብብህክ) በወይላታ ዞን ከነሀሴ 3-5፣ 2012 ዓ.ም በተቀሰቀሰ አመጽ፣ የጸጥታ ሀይሎች፣ ሁለት አልፎ-ሂያጆችን ጨምሮ፣ 16 ሰዎችን ገድለዋል። 20 የሚሆኑ የወላይታ ዞን የአስተዳደር ሀላፊዎችን፣ የማህበረሰብ መሪዎችንና አክቲቭስቶችን መታሰር በመቃወም ወደ አደባባይ የወጡ ሰላማዊ ሰልፈኞች፣ በጸጥታ ሀይሎች[1] በጥይት ተመትተዋል፤ ተደብድበዋል።

## ሀሳብን በነጻነት የመግለጽና የመሰብሰብ መብት

በጥር ወር፣ መንግስት  አዲስ የጸረ-ሽብር ህግን አጽድቋል። ምንም እንኳ ህጉ በሽብር ወንጀል የታሰሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን መብት የሚይያስጠብቁ አንዳንድ የተሻሻሉ አንቀጾችን ቢያካትትም፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቶችን የሚገድቡ አንዳንድ አንቅጾችም አሉበት። በተወካዮች ምክር ቤት፣ በመጋቢት ወር የጸደቀው የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ፣ ሰዎች ሀሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው ወንጀለኛ ያደርጋቸዋል።

የጸጥታ ሀይላት፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽንና የመሰብሰብን መብት በማፈን ጥቃት ፈጽመዋል። የካቲት 7፣ 2012 ዓ.ም የኦሮሞ ነጻነት ግምባር (ኦነግ) የተሰኘ የተቃዋሚ ፓርቲ፣ በኦሮሚያ ክልል በምትገኝ የወልንጪቲ ከተማ ጽህፈት-ቤቱ ውስጥ የምረቃ ስነ-ስርአት ላይ እያለ፣ የክልሉ ልዩ ሀይሎች ቢሮውን በርግደው ገብተው ጥቃት ፈጽመዋል። ተሳታፊዎች ላይ ጥይት በመተኮስና በአስለቃሽ ጭስ በመበተን፣ አንድ  የኦነግ ደጋፊን ሲገሉ፣ ሌሎችን ደግሞ ደብድበዋል። የኦሮሚያ ዜና ኔትወርክ ንብረት የነበረውን የአንድ ተሸከርካሪ ጎማዎችን በጥይት ከበሳሱ በኋላ፣ መሳሪያዎቻቸውንም ቀምተዋቸዋል። በዚያው ቀን፣ የክልሉ የልዩ ሀይል አባላት፣ ቡራዩ ከተማ በምትገኝ ሆቴል፣ ለምረቃ የተገኙ የኦነግ ደጋፊዎችን በሀይል በመበተን፣ አንድ ሰው ሲገድሉ፣ ለሎች በርካታ ደጋፊዎችን ደግሞ አቁስለዋል። 30 የሚሆኑትን በፖሊስ መኪና አስገድደው ጭነው ወደ ቡራዩ ስታዲዩም በመወሰድ ደግመው ደጋግመው ከቀጠቀጧቸው በኋላ፣ በጉልበታቸው[2] እንዲሄዱ አድርገዋቸዋል።

## በዘፈቀደ የሚፈጸሙ እስራቶች

ባለስልጣናት፣ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ላይ ክስ ሳይመሰረትባቸውና ለፍርድ ከመቅረባቸው በፊት፣ ለእስር (አንዳንዴም ለረጅም ጊዜያት) ይዳርጓቸዋል። ምንም እንኳን ፍርድ ቤቶች በየጊዜው ነጻነታቸውን በመጠቀም ተቃዋሚ ፖለቲከኞች በዋስ ከእስር እንዲለቀቁ ቢያደርጉም፣ ፖሊስ በተደጋጋሚ የፍርድ ቤት ትዕዛዞችን ሲጥስ ታይቷል።

---

[1] *Ethiopia: Stop the use of deadly force on protesters* (Press release, 14 August)

[22] *Ethiopia: Vendor killed, musician injured after police attack opposition supporters in Oromia* (Press release, 17 February)

በጥር ወር፣ ፖሊስ ቢያንስ 75 የሚሆኑ የኦነግ ደጋፊዎችን በኦሮሚያ ክልል አሰሯል። አብዛኞቹ ክስ ያልተመሰረተባቸውና ለ[አያሌ] ወራት ዳኛ ዘንድ ያልቀረቡ ነበሩ። ከእነዚህም መካከል ሜልቱ ታከለ የተባለች ታዋቂ የፖለቲካ አክቲቪስት አንዷ ስትሆን፣ በየካቲት ወር ከእስር ብትፈታም፣ ሀምሌ መጀመሪያ ላይ እንደገና ታስራ፣ ሀጫሉ ሁንዴሳ የተባለ የኦሮሞ ሙዚቀኛ መገደልን (ከታች እንደተገለጸው፣ ህግ-ወጥ ግድያን) ተከትሎ  የተቀሰቀሰውን አመጽ አነሳስተሻል የሚል ክስ ተመስርቶባታል። በነሀሴ ወር፣ አመጽን በማነሳሳት ክስ የዋስ መብት ተጠብቆላት ከእስር ተለቃለች።

በየካቲት ወር፣ የጸጥታ አካላት፣ አምስት ከፍተኛ የኦነግ አመራር አባላትንና አራት ደጋፊዎችን አዲስ አበባ ውስጥ አስረዋል። ከነዚህ መካከል ስምንቱ በ24 ሰአት ውስጥ ተፈትተዋል። ሁለት የኦሮሚያ ዜና ኔትዎርክ ጋዜጠኞችና ሶስት የኦነግ ባለስልጣናት የቡራዩን ፖሊስ ጣቢያ ፎቶ አንስታችኋል በሚል ክስና በትራፊክ ህግ ጥሰት ሳቢያ በመጋቢት ወር ለእስር ተዳርገዋል። ምንም እንኳን አቃቤ ህግ የኋላ ኋላ የተከሰሱበት ጉዳይ ከወንጀል ድርጊት ጋር ተያያዥነት የለውም ብሎ ክሳቸውን ቢያነሳም፣ ፖሊስ ያቀረቡት የማንነት ሰነድ ህገወጥ ነው በሚል በእስር እንዲቆዩ አድርጓል። አራቱ ምንም አይነት ክስ ሳይመሰረትባቸው በግንቦት ወር ሲለቀቁ፣ ባትር ፊሊ የተባለው ሌላኛው ታሳሪ ግን ምንም ክስ ሳይመሰረትበት እስከ ታህሳስ ወር መጨረሻ በእስር እንዲቆይ ተደርጓል።

## ኢፍትሀዊ የፍርድ ሂደቶች

ጥቅምት ውስጥ፣ መንግስት፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትን ህግ ለመተካት የሚያስችል የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት መረጃ የተሰኘ የህግ ረቂቅ አቅርቧል። የረቂቅ ህጉ አላማ እየተጓተቱ የሚያስቸግሩ ፍትህ ነክ ችግሮችን ለመቅረፍ ሆኖ ሳለ፣ የህጉ አንዳንድ አንቀጾች የአለም አቀፍ ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት ደረጃዎችን የማያሟሉ ናቸው።

## ህገ-ወጥ ግድያዎች

በስፋት በተንሰራፋው ብሄር ተኮር ነውጥና ጥቃት የተነሳ በሙቶ የሚቆጠሩ ሰዎች በታጣቂ ቡድኖች ተገድለዋል።

በሰኔ 22 ቀን፣ የታዋቂውን የኦሮሞ ሙዚቀኛ ሀጫሉ ሁንዴሳን መገደል ተክትሎ፣ ከሰኔ 23 እስከ 24 በኦሮሚያ ክልል በተቀሰቀሰ ሁከት፣ 166 ሰዎች ተገድለዋል። የሀጫሉ መገደል፣ በአዲስ አበባ እና እንደ ሀረርና ድሬዳዋ ባሉ የተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች ህዝባዊ ተቃዋሞወችና ሁከትን አስነስቷል። የተደራጁ ወጣቶች፣ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን ጨምሮ፣ አናሳ የብሄርና የሀይማኖት ማህበረሰቦችን ኢላማቸው አድርገዋል። በዚህም የተነሳ፣ በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች ቢያንስ 40 የሚሆኑ ሰዎች ተገድለዋል፤ ንብረታቸውም በእሳት ጋይቷል። በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች በተቃዋሚ ሰልፈኞችና በጸጥታ ሀይሎች መሀል በተፈጠሩ ግጭቶች፣ የጸጥታ ሀይሎች አድማውን ለመበተን በተኮሱት ጥይት ከሙቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ተገድለዋል። የፌደራሉ ፖሊስ ባለስልጣናት እንደሚሉት፣ ሁለት የፖሊስ መኮንኖችን ጨምሮ፣ 10 ሰዎች በቦምብ እና በጥይት ህይወታቸውን አጥተዋል። በህገወጥ ግድያዎችና ንብረት በማውደም ወንጀል የተጠረጠሩ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ጨምሮ፣ 5000 የሚሆኑ ሰዎች ታስረዋል። በመስከረም ወር፣ በተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፣ በጃዋር መሀመድ፣ በበቀለ ገርባ እና በእስክንድር ነጋ ላይ የጠቅላይ አቃቢ ህግ ጽህፈት-ቤት የሽብር ወንጀል ክስ መስርቶባቸዋል። በጥቅምት ወር፣ በሀጫሉ ሁንደሳ ግድያ ተጠያቂ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ አራት ሰዎች የሽብርና የግድያ ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው ታስረዋል።

መስከረም ውስጥ፣ የክልሉ ፖሊስ፣ የቤኒሻንጉል ህዝብ የነጻነት ግምባር አባላት ናቸው ብሎ የፈረጃቸው ታጣቂ ቡድኖች፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚኖሩ የአማራና የአገው ተወላጆች ላይ በፈጸሙት ተከታታይ ጥቃት ቢያንስ 45 ሰዎች ሲገደሉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል።

ከጥቅምት 8 እስከ ጥቅምት 11፣ 2013 ዓ.ም ባሉት ቀናት፣ በደብብህከ፣ ጉራፈርዳ ቀብሌ የሚኖሩ ቢያንስ 31 የሚሆኑ የአማራ ብሄር ተወላጆች በታጣቂ ሀይሎች ሲገደሉ፣ 1500 የሚሆኑ ደግሞ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል[3]።

ጥቅምት 30 ቀን፣ የአካባቢ ሚሊሻዎችና ወጣቶች፣ በምዕራብ ትግራይ[4]፣ ማይካድራ በተባለ ቦታ የሚኖሩ በርካታ(በሙቶዎች የሚቆጠሩ) ተወላጆችን በጩቤ በመውጋትና በመቆራርጥ ገድለዋቸዋል። የአይን እማኞች፣ የሟች አስከሬኖች ላይ ጩቤና ገጀራ ያረፈባቸው የተተለተሉ አካላት እንዳዩ ይናገራሉ። ከጥቃቱ የተረፉት ደግሞ፣ የትግራይ ክልል መንግስት ታማኝ ባለሟል የሆኑ የጸጥታ ሀይል አላፊዎች ጥቃቱን እንደፈጸሙት ይናገራሉ።

---

[3] *Ethiopia: Authorities ban protests as "illegal and unnecessary"* (Press release, 27 October)

[4] *Ethiopia: Investigation reveals evidence that scores of civilians were killed in massacre in Tigray state* (Press release, 12 November)

## ከመኖሪያ ቤት አስገድዶ ማስውጣት

በየካቲት ወር መጀመሪያ፣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በርካታ ቤቶችን በማፍረስ፣ በኮቪድ-19 ወረርሺኝ ጊዜ፣ ቢያንስ አንድ ሺህ የሚሆኑ ሰዎችን ቤት-አልባ አድርገዋቸዋል። ነዋሪዎቹ፣ ቤታችንን የሰራነው በ1999 ዓ.ም በገዛነው መሬት ላይ ነው ሲሉ፣ ባለስልጣናቱ ግን ነዋሪዎቹ የሰሯቸው ቤቶች ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባልተገዙ መሬቶች የተገነቡ የጨረቃ ቤቶች ናቸው ይላሉ። ይሁንና፣ ቤቶቻቻው የፈረሱባቸው ሰዎች፣ ከቤታቸው እንደሚወጡ የቅድሚያ ማስጠንቀቅያ አልተሰጣቸውም ወይም ማሳሰቢያ አልተነገራቸውም። አብዛኛዎቹ ይተዳደሩ የነበሩት መደበኛ ባልሆኑ የኢኮኖሚ መስኮች ስለነበረ፣ ኮቪድ-19ን ለመከላከል በተወሰዱ እርምጃዎች የተነሳ የስራ እድላቸው ተመናምኗል።

የመኖሪያ ቤቶቻችውን መፍረስ ተከትሎ፣ ተፈናቃዮቹ ኬንዳና ላስቲክ በመጠቀም በጊዚያዊነት ለመኖር የሚያስችሏቸውን መጠለያዎች ለመስራት ሞክረው ነበር፤ ይሁን እንጅ፣ እነዚህም ጊዚያዊ መጠለያዎች ሚያዚያ 6 ቀን፣ በባለስልጣናቱ ትዕዛዝ ፈርስው፣ የተሰሩባቸው ቁሳቁሶችም ለፖሊስ ገቢ ሆነዋል። በዚህም የተነሳ፣ የቤተሰብ አባላቱ፣ በክረምት ምድር ጎዳና ላይ ፈሰው ዶፍ ዝናብ እበላያቸው ላይ ሲውርድባቸው ባጅቷል።

## እውነትን፣ ፍትህንና፣ ካሳን የማግኘት መብት

በህዳር ወር 2001 ዓ.ም በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ ይማሩ የነበሩና ባልታወቁ ሰዎች ታፍነው የተወሰዱ ተማሪዎች ያሉበትን ሁኔታ እና እነሱንም ለማስለቀቅ መንግስት ምን አይነት እርምጃ እንደወሰደ፣ እስከአሁን ባለስልጣናቱ ምንም መረጃ አልሰጡም። [እስከ ታህሳስ መጨረሻ ድረስ ታፋኞቹ የት እንደአሉ የሚታወቅ ነገር አልነበረም][5]

ከህግ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎችን፣ ማሰቃየትና ለሎች መጥፎ አያያዞችን እና የጅምላና የዘፈቀደ እስራቶችን ጨምሮ፣ ከ1983ዓ.ም አንስቶ ይፈጸሙ ስለነበሩ ሰቆቃዎችና አሳዛኝ የሰብዓዊ ጥሰቶች ሀላፊነት መቀበልን/መውሰድን በተመለከተ መንግስት አንዳንድ እርምጃዎችን ወስዷል። ይሁን እንጂ፣ የእነዚህ ወንጀሎች ሰላባ በሆኑ ተጠቂዎች ዘንድ፣ የግድያ ወንጀሎችን፣ ማሰቃየትንና ለሎች መጥፎ አያያዞችን እና ከመጠን ያለፈ ህይልን የጠቀሙ ወገኖች፣ ማለትም የኢትዮጲያ የመከላከያ ሀይል፣ የፌደራል ፖሊስ እና የክልል ልዩ ፖሊስ ሀይሎች፣ ለፍርድ ይቀርቡልናል የሚል የተስፋ ጭላንጭል የለም።

[5] *Ethiopia: Parents fear for missing Amhara students as universities close over COVID-19* (Press release, 25 March)